# የባሕር-በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ፤

*የግል አስተያየት:- አያል ሰው ደሴ - ክፍል አራት*

ጉዳዩን በዚኽ መልክ ለማየት አስተዋይነቱ፣ ድፍረቱና ቁርጠኝነቱ ካለ፣ ከሥር-መሠረቱ የአብዛኛው ውስጣዊ ችግሮቻችን ምንጭ የሆኑ የውጭ ባዕዳን ለራሣቸው ዓላማ ሲሉ በሁለቱ መኻል ልዩነት እንዲሰፋ፣ እርስ-በርስ መናቆር እንዲቀጥል ለሚያደርጉት የተለመደ መሠሪ እርምጃ በር ይዘጋል:: አሁን ያለው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ የውጭ ተፅዕኖን የሚጋብዝ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተፈቀደ ግን የኤርትራ ሕዝብ የተሻሻለና የተረጋጋ ሕይዎትን ማግኘቱ ቢያንስ አጠራጣሪ ይሆናል::

የውጭ ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት በተፈጥሮው የሕዝብ አንድነትንና ውስጣዊ ሰላምን አደፍራሽ በመሆኑ፤ ኤርትራ ያላትን የኤኮኖሚ አቅም የሕዝቡን ኑሮ በማሻሻልና ደኅንነቱን በመጠበቅ ላይ በዋል ፈንታ በቀጣይነት ፀጥታዋን በማስከበርና የውስጥ ውጥረትን በማርገብ ሙከራ ላይ እንድታውል ትገደዳለች:: ይኽን ለማድረግ በሚደረግ መጠመድ ደግሞ አሁን ባለው ውጥረትና ሽሚያ በተበራከተበት፣ ይበልጥ መሣሪያ ነካሽና በትጥቅ ጎልብቶ ለመገኘት ሩጫ በበዛበትና አክራሪ አዝማሚያዎች በተበራከቱበት አደረኛ የዓለም አካባቢ ከአንድ ሽህ ኪሎ-ሜትር በላይ እርዝመት ያለውን የቀይ ባሕር ጠረፍ ኤርትራ ብቻዋን አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መጠበቅ፣ ፀጥታዋን ማስከበርና ከውጭ የሚቃጣን ጦርነት ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ለማግኘት በጣሙን ይቸግራታል:: ቢያንስ-ቢያንስ ኤርትራ ያለ-የሌለ የምጣኔ ሃብት አቅሟን በዚሁ ጉዳይ ላይ ማዋል ስለምትገደድ የኤርትራን ሕዝብ በሚጠቅሙ የግንባታና የእድገት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳትሠለፍ እክል ሊሆን እና የኅብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎቶች ጭምር ለማሟላት እንዳትችል ሊያደርጋት ይችላል:: ያ ደግሞ በራሱ ሕዝብን እየከፋ ለሚሄድ ችግር ሊዳርግ፣ ሕዝብም ተስፋ እንዲቆርጥና አመኔታውን እንዲያጣ ስለሚያደርግ፣ ለአክራሪነት አዝማሚያዎች በር ሊከፍት፣ አልፎም እንዲጎለብቱ ዕድል ይሰጣል:: በርካታ ገጽታዎች ያሏቸው ችግሮች እየተደጋገፉ የመከራው አዙሪት እንዲቀጥል ሁኔታን ያመቻቻል:: ያም በተራው ልዩ-ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ባሰ ውስጣዊ ውጥረት ጎትቶ ስለሚያስገባ ሁሉንም ጎጂ የሆነ ሰላምና መረጋጋት አደፍራሽ ቀውስ ሊፈጠር ይችላል::

የኤርትራ ሰላምና መረጋጋት በአስተማማኝ ሁኔታ መረጋገጡ ደግሞ የሚመለከተውና የሚያገባው አሁን ተለይታ ላለችው ኤርትራ ብቻ ሣይሆን ለኢትዮጵያ ጭምር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: ውስጣዊ ሰላሟን ያጣችና ሕዝቧን ሐይማኖትን፣ ጎሣንና አካባቢን መሠረት ሳደረገ ትርምስ የምትዳርግ ኤርትራ በቀጥታ ለኢትዮጵያና ከዚያም አልፎ ለአካባቢው ጠንቅ እንደሚሆን አጠያያቂ አይሆንም:: ወገን የሆነው የኤርትራ ሕዝብ እንደዚኽ ዓይነት አስከፊ ዕድል እንዳይደርስበት ከወዲኹ ከጎኑ መቆም ግዴታ ይሆናል:: ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ግዴታ ይሆናል::

**ስለ-ሆነም ኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄን ስታነሣ ግልጥ ከሆነው የብሔራዊ ጥቅሟን ማስከበር አኳያ ብቻ ሣይሆን በአቶ ኢሣኢያስ አፈወርቂ ሽዓብያ ጠባብ እስር-ቤት የሚገኘውን ወገናችን የኤርትራ ሕዝብ ከሚገኝበት የአፈና ይዞታ ተላቅቆ፣ መብቶቹ ተከብረውለት፣ ሰብአዊ ክብሩ ተረጋግጦለት እንደ ጥንቱ በቀረው የኢትዮጵያ ክፍል በነፃነትና በእኩልነት ለመሥራትም ይሁን ለመኖር ከሚፈጥረው ተያያዥና የማይነጣጠል ዕድል ጋር ተዛምዶም ሊታይ ይገባል እላለሁ::**

ቀደም-ሲል እንደጠቀስኩት *“የኤርትራ ሕዝብ እንዴት መኖር እንዳለበት የኤርትራዊያን ጉዳይ ነው፣ ሌሎቻችሁ ምን አገባችሁ?”* የሚሉ ወገኖች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው:: ሆኖም ቢያንስ-ቢያንስ የኤርትራ ሕዝብ ደኅንነቱና ሰላሙም ሆነ ጉዳቱና ሰላም ማጣቱ በቀጥታ የሚመለከተንና ሰላም ማጣቱ ሰላማችንን እንደሚነሣ፣ ፀጥታውና ደኅንነቱ ከፀጥታችንና ከደኅንነታችን ጋር የተሣሰረ በመሆኑ፣ ከአፈና ያልተላቀቀ እና ይበልጥም ለባሰ አደጋ የተጋለጠ ሕዝብ፣ ያውም ወገን የሆነ ሕዝብ፣ ጉዳይ ደግሞ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ያገባዋልና ነው ኢትዮጵያውያን የኤርትራን ጉዳይ ጉዳያችን ብለው የሚመለከቱትና ሊመለከቱት የሚገባው::

በእርግጥ ከፍ-ሲል እንደተጠቆመው *“ኤርትራ ዓለም-አቀፍ እውቅና ያላት ስለ-ሆነ ሕዝቡ ከኢትዮጵያ ጋር እንደገና አንድ ለመሆን ፍላጎቱን በግልጥ እስከሚያሣውቅና ጥያቄ እስከሚያቀርብ አሁን ምንም ማድረግ አይቻልም”* ከሚል እስከ *“አንዴ ፈልገው ሄደዋልና እንደ-ፈለጉ ይሁኑ”* የሚል አስተሣሰብ እንደማይጠፉ ይታወቃል:: በተጨማሪም በሁለቱም በኩል ያሉ አንዳንድ ወገኖች አሰብን ኢትዮጵያ በባለቤትነት ብትቆጣጠር ኤርትራ ትጎዳለችና መሆን የለበትም እንደሚሉ ይታወቃል:: እነኚኽ አስተሣሰቦች ግን አንድም ከመጠን በላይ ካለፈ ሕገኛ ጥንቁቅነት ሌላም ከቁጭትና ከእልኽ የመጣ እንጂ ያለው ሁኔታ ባለበት መቀጠል ጨርሶ እንደማይችልም ሆነ እንዲቀጥል ከተደረገ በሁለት በተከፈለው ሕዝብ የጋራ ዘለቄታዊ ጥቅሞች፣ በሁለቱም አጠቃላይ

ሰላም፣ መረጋጋት፣ ሉዓላዊነት፣ ብሔራዊ ደኅንነትና ኅልውና ላይ የሚያስከትለውን አደጋና ችግር ሁሉ በሚገባ ካለማጤን የሚያልፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል የሚቀርበው ክርክር ኢትዮጵያ የራሷ ወደብ ቢኖራትም (ለምሣሌ አሰብ)፣ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን አደጋዎች ሁሉ ልታስቆም አትችልም የሚል ነው፡፡ እንደ-እኔ ይኽ ክርክር አጉልኛ ነው፡፡ ለምሣሌ በባሕር የተከበበችው እንግሊዝ በናዚዎች ከመጠቃት፣ ጃፓኖችም በምዕራባውያን ኃይሎች ከመቸነፍ እንዳልዳኑ ሁሉ ኢትዮጵያ በራሷ ቁጥጥር ሥር በባለቤትነት የምታዝበት የባሕር በር/ወሰን ቢኖራት በራሷ ላይ የሚቃጡ አደጋዎችን ሁሉ ሙሉ-በሙሉ መከላከል ትችላለች ማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም በወደቦቿ ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት እንድታጣ ከተደረገ ጀምሮ የገጠማትን የወደብ ፍለጋ መንከራተት፣ በባዕዳን በጎ-ፈቃድ ላይ ብቻ የወደቀ ያልተመቸና ጥገኛ አገልግሎት፣ ለዚሁ አገልግሎት በውጭ ምንዛሬ የሚከፈለው ገንዘብ፣ የራሷ የባሕር-ኃይል እንዳይኖራት መደረግና ያ ደግሞ ከአገራዊ ክብሯ ጀምሮ በውስጣዊ ደኅንነቷና ፀጥታዋ ላይ ያስከተለውና እየጨመረ የሚሄድ አደጋ፣ ከዚሁ የባሕር-ኃይል ባለቤት ካለመሆን ጋር ተያይዞ የታጣው የባሕር ላይና የባሕር ውስጥ የሣይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ዕድል፣ ወዘተ.. ሚዛን ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ የባሕር በር ባለቤት መሆን ግን ኢትዮጵያ ቢያንስ ቢያንስ አሁን ካለችበት በእጅጉ የተሻለ ደረጃ ላይ እንድትሆንና ይበልጥም ችግሮቿ እየተባባሱ፣ እድገቷም ጥገኛ ከመሆንና በሌሎች በጎ-ፈቃድ ላይ እንዳይወድቅ ማድረግ ከመቻል ባሻገርና ከራሷም አልፋ በአሁኑ ጊዜ በባሕር ላይ ጠላፊ አሸባሪዎች (ፓይረትስ) የሚደርሰውን አደጋ በመቅረፉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ለቀረውም ዓለም ሣይቀር ልትታደግ በቻለች፡፡

ኢትዮጵያ አሰብን በባለቤትነት፣ ምፅዋን ደግሞ በሚደረግ የጋራ ስምምነት ብትጠቀም በሁለቱ ተለያይተው የማይለያዩና የተሣሰሩ ወገኖች መኻል ያለው ግንኙነት ወደብን በመፍቀድና ባለመፍቀድም ይሁን በአጉል ጊዜያዊ ጥቅም ወይም ችግሮች ላይ የተንጠለጠለ ሣይሆን ከዚያ በላይ ባሉ የጋራ ፀጥታንና ኅልውናን ማረጋገጥ ላይ እንዲመሠረት ስለሚያደርግ ትሥሥሩ ሁለቱንም ወደሚጠቅም የጋራ እድገትና ልማት አስተሣሰብና ቅኝት ሊያድግ ያስችላል፡፡ ያ ሲሆን ደግሞ ያለፉ በጠላትነትና በጥርጣሬ የመተያየት ሁኔታዎች እየተቀረፉ መተማመን እንዲዳብር፣ ሕዝብ ለሕዝብ ያለው ግንኙነት ነፃና እቀባ-የለሽ ሆኖ መዘዋወርና በሁሉም ዘርፍ የሙያና የንግድ ልውውጥ ማድረግ ስለሚያስችል፣ በጋራ የወል ጥቅሞች ላይ ይበልጥ ትኩረት በመስጠት መቀራረብን ሊያስከትልና ከተራ ግንኙነት ለአለፈ አዲስ የአብሮነት ትሥሥርና አንድነት ምዕራፍ ለመጀመር የተሻለ ዕድል ይሰጣል፡፡

ሁለተኛ ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው እነዚኽን የባሕር በሮች ኢትዮጵያ እንዳትጠቀም ማድረግን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ልዩ ልዩ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሚሹ የውጭ ኃይሎች በሁለቱ ወንድማማች/እትማማች ሕዝብ መኻል ይበልጥ አለ-መግባባት እንዲፈጠር ለሚያደርጉት እኩይ ሴራ የማይመችና በዚኹ ሰበብም ጣልቃ እንዳይገቡ በር ይዘጋል፡፡ ከዚኽ በላይ እንደተባለው ኤርትራ በርካታ ውስጣዊ ውጥረቶችንና ችግሮችን፣ አካባቢያዊና ዓለም-አቀፋዊ ተጋፊና አሉታዊ ጫናዎችን ተቋቁማ ለብቻዋ እንደ-አገር ለመቀጠል የሚጠይቀውን ከፍተኛ ጥሪትና የኤኮኖሚ አቅም ብቻዋን መሸከም አትችልም፡፡ ያ ደግሞ በታታሪነቱና በፈጠራ ችሎታው የታወቀው የኤርትራ ሕዝብ ችግሮቹን ለመወጣት ጥረት አያደርግም ማለት ሣይሆን የችግሮቹ መጠን፣ ስፋትና ጥልቀት በውስጥ ካለው የውስጥና አካባቢያዊ ውጥረት እንዲሁም የጥሬ ሃብት እጥረት ጋር ተደማምረው ሁኔታውን ጨርሶ ከአቅም በላይ ስለሚያደርገው ነው፡፡

ስለ-ሆነ አንድም በኤርትራ ቁጥጥር ሥር ያሉ ወደቦች አሁን ባሉበት ሁኔታ ሙሉ ጥቅም ሣይሰጡ ቦዝነው እንዲቆዩ መፍቀድ ይሆናል፡፡ ያ ደግሞ ጨርሶ አያዋጣም፡፡ ያንን ማድረጉ ስለማያዋጣና ጥቅም ስለ-ሌለው ደግሞ ኃላፊነት የማይሰማቸው ለሕዝብ አሣብና ተሣትፎ ደንታ የሌላቸው እነ አቶ ኢሣኢያስ ወይም የነሱን መሥመር የሚከተሉ የሸዓብያ መሪዎች ለጊዜአዊ የኤኮኖሚ ጠቀሜታ ወይም ደግሞ በቅርብ የሚፈልጉትን ለማግኘት በማለም ኢትዮጵያን ለማፈንና ለማስጨነቅ ከአለ ትንሽ አስተሣሰብና ከይሲ ስሌት ተነስተው እነዚኽን እጅግ ስትራቴጂያዊ ዋጋና ጠቀሜታ ያላቸው ወደቦች ለባዕዳን የጦር ሠፈር አገልግሎት እንዲውሉ “ማከራየትን” ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው ጥቅመ-ቢስ መሆኑ ቢታወቅም ይኽ ሁለተኛው መንገድ ግን የኤርትራን ሕዝብ እየቆየ እሱነትንና ክብሩን ለሚጋፉ የባዕዳን ተፅዕኖዎች አጋልጦ የሚሰጥና የውጭ ኃይሎች መራኮቻና መፋለሚያ መድረክ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

ስለሆነም ከሁለቱም ይልቅ የኤርትራን ሕዝብ የቅርብም ይሁን ዘለቄታዊ ጥቅሞች ማስጠበቅ የሚያስችለው ቀደም-ሲል የተጠቀሰው አሰብን ኢትዮጵያ በባለቤትነት እንድትቆጣጠርና ምፅዋን በስምምነት እንድትገለገልበት ማድረጉ ይሆናል፡፡ እንደኔ እንደኔ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ በቀጥታ ባለቤትነት እንድትቆጣጠር ማድረጉና ምፅዋን (ካስፈለገም አሁን አገሪቱ የምትጠቀምባቸውን የባዕዳን ወደቦች አገልግሎት ሁሉ ወደዚኽ በማዘዋወርና ለነዚያ የሚከፈለው በቀጥታ ለኤርትራ

እንዲሰጥ በማድረግ) በስምምነት መጠቀሙ ሁለቱም ወገኖች በሁሉም ረገድ ማለት በኤኮኖሚው፣ በፖለቲካው በሰላምና መረጋጋት ረገድ አትራፊ ይሆናሉ:: ከዚያም አልፎ ለጋራ ፀጥታቸውና ኀልውናቸው ዋስትናነት ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያገኙበትን ዕድል ይሰጣል::

ኢትዮጵያ በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር በር/ጠረፍ ያስፈልጋታል አያስፈልጋትም ከሚለው ይበልጥ ትልቁ ጥያቄ እንዴት ነው ያንን ማድረግ የሚቻለው? የሚለው መሆኑ ግልጥ ነው:: ለጥያቄው ክብደት የሚሰጠውና የሚታየው ደግሞ በሌጣው ሣይሆን ጉዳዮችን በሰከነ፣ የሕዝብን ጥቅም ባስቀደመ፣ የዜጎችን እሣቦትና ፍላጎት ቁጥር ውስጥ ባስገባ ማየት በሚሣናቸው፣ ከምንምና ከማንም በላይ በሥልጣን መቆየትን ቅድሚያ ያደረጉ፣ የችግሮች መፍትኄ ከውይይትና ከመግባባት የሚገኝ ሣይሆን በጉልበት ብቻ ከሚመስላቸው በአሁኑ ጊዜ አዲስ አበባና አሥመራ ሥልጣን በጨበጡ ሁለት አምባገነኖች ተፈጥሮ፣ ሁኔታና ይዞታ አኳያ እንደሆነ እገምታለሁ:: በቀይ-ባሕር በኩል የሚነሣ የባሕር በር ጉዳይ በሁለቱም በኩል ያለው ሕዝብ ከሚያስፈልገው አስተማማኝ ሰላም፣ የመብቶች መከበር፣ የፍትኅ መስፈንና የዴሞክራሲያዊ ለውጥ ጥያቄ ተለይቶ አይታይም:: በመሆኑም የእነዚኽ እሴቶች እውን መሆንና አለ-መሆን በአሁኑ ጊዜ በሁለቱም ሕዝብ ጫንቃ ላይ ያንሠራፉ አምባ-ገነኖች ከሥልጣን መወገድ ጋር የተዛመደ ነው::

**መደምደሚያ፤**

ከዚኽ በላይ ኢትዮጵያ ለምን በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር-በር/ጠረፍ እንደሚያስፈልጋትና ይኽንንም በሰላማዊ መንገድ እንዴት እውን ማድረግ እንደሚቻል አጠር አድርጌ ለመዳሰስ ሞክሬአለሁ:: ይኽንን አንገብጋቢ፣ ሆኖም አወዛጋቢነቱ ግልጥ የሆነ ዓብይ ጉዳይ እንደ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ-ማርያም በመሰሉ አስተዋይ ምኁራን ረዘም ላለ ጊዜ ሲነሣና በዝርዝር ሲታይ የነበር፣ አሁንም ልዩ ትኩረት የሰጡትና የሚሰጡት እንደሆነ ይታወቃል:: በዚኽ ጽሑፍ ጉዳዩን በአጭሩ ለማየት የሞከርኩት አሁን ኤርትራ የምትገኝበት ሁኔታ እስከ-ወዲያኛው መቀጠል ካለመቻሉ፣ እንዲቀጥል ከተደረገ ከኤርትራ ሕዝብ ሉዓላዊነት፣ መብቶች መከበር፣ ሠረታዊ ሰብዓዊ ክብር መጠበቅ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ፀጥታና ደኅንነት ላይ ከሚያስከትለው ዘርፈ-ብዙ አደጋ፣ የአፋር ሕዝብ ተከፋፍሎ መቀጠሉ በምንም መንገድ ተቀባይነት የሌለው፣ መቀጠል የሌለበትና ፍትኅ-ኀደል ድርጊት ከመሆኑ፣ ፍላጎቱ ከቁጥሩ ጋር እያደገና እየጨመረ የሚሄደው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታፍኖ መቀጠሉ ጨርሶ ተቀባይነት እንደማይኖረው በረጅም ጊዜ ታሪኩ የባሕር በር ባለቤትነት እጦት ካስከተለበት አጠቃላይ ውድቀት መራር ልምድ በመነሣት አሁንም በአገሩ ብሔራዊ ደኅንነት፣ በሰላሙና መረጋጋቱ፣ በነፃነቱ፣ በሉዓላዊነቱ፣ በኅልውናው፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በሚያደርገው ትግል፣ በወደፊት ልማትና ብልፅግናው ላይ ከሚኖረው እርባና፣ አስፈላጊነትና ሚና አኳያ ነው::

መውጫ-መግቢያዋ የታፈነው ኢትዮጵያ በባለቤትነት የምትቆጣጠረው የባሕር በር እስከሌላት ድረስ ምንም ዓይነት አስተማማኝ ልማት ላይ ልትሠማራም ሆነ፣ ሉዓላዊነቷን፣ ብሔራዊ ክብሯን፣ ደኅነቷንና ፀጥታዋን ከባዕዳን መተናኮስ በብቃት ለመከላከል አዳጋች እንደሚሆኑባት ግልጥ ይመስለኛል:: ያ ደግሞ በቀጥታ ሕዝቧ የአምባ-ገነን ሥርዓቶችን አዙሪት ሰብሮ የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን በሚያደርገው ትግልና ጥረት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ሊታወቅ ይገባል:: ኢትዮጵያ ደኅንነቷ፣ ሰላሟና እድገቷ ለአደጋ ከተጋለጡና ሕዝቧ ሙሉ ነፃነቱ ካልተከበረ፣ አንድነቱ በየጊዜው የሚደማ ከሆነ ደግሞ ኤርትራ ሰላምም ሆነ መረጋጋት፣ ሕዝቧም ዴሞክራሲና እውነተኛ ነፃነት ይኖሩታል ብሎ ማሰቡ ዘበት ነው:: ስለሆነም የአንዱ ደኅንነትም ሆነ ጉዳት ከሌላው ጋር በቀጥታ የተሣሰረና የተዛመደ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

መቼም የኤርትራን መገንጠል አጥብቀው ከሚያወግዙና በጉልበት ከሁለት ተከፍሎ ያለው ሕዝብ ዞሮ-ዞሮ ሁኔታዎች ቢመቻቹና ሕዝብ በነፃ የመወሰን መብቱ ቢረጋገጥለት አብሮ መኖርን እንደሚመርጥና ይዋል-ይደር እንጂ ተመልሶ አንድነቱን እንደሚያረጋግጥ ከማይጠራጠሩት ውስጥ እኔ አንዱ ነኝ:: ታዲያ ይኽን አቋም ይዠ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ በባለቤትነት የመቆጣጠር መብቷን ማስከበር አለባት ስል ተቃርኖ ያለበት አጉልኛ ክርክር ተደርጎ በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ቢታይ አይገርመኝም:: **ሆኖም እኔ የአሰብን ወደብ ኢትዮጵያ በባለቤትነት የመቆጣጠር መብቷ መከበር አለበት ስል የኤርትራን ጥቅም ጨርሶ በማይጋፋበትና አልፎም ሁለቱንም በጋራ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግና ዞሮ-ዞሮ ተመልሶ አንድ ላይ ከመኖር ውጭ ሌላ የተሻለ አማራጭ ከሌለውና ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በአሁኑ ጊዜ ከሁለት እንዲከፈል የተደረገው የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላምና በመግባባት ወደ ተሻለ የአንድነት ትሥሥር የሚወስድ ሰላማዊና የመጀመሪያው መንገድ ነው ብየ ስለማምን እንጂ ያ በራሱ መዳረሻና የመጨረሻ ግብ ነው ከሚል ግንጥል አስተሣሰብ ላይ ተነስቸ አይደለም::**

በኢሣኢያስ አፈወርቂ የአፈና አገዛዝ ሥር የወደቀውና መፈናፈኛ ያጣው የኤርትራ ሕዝብ የሚገኝበት እየፈላ ያለ የውስጥ ውጥረት ወደ-አጠቃላይ ትርምስ የሚወስድ አደገኛ ፍንዳታ ጫፍ ላይ መሆኑና ኤርትራውያን የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለሚጋብዝ አደጋ የተጋለጡ በመሆናቸው የአለው ይዞታ እንዲቀጥል ከተፈቀደ ከአንዲት የአሰብ ወደብ የበለጠ ሊያጡ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር የመቻሉን ምናልባታዊነት በተገቢ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው እላለሁ፡፡ በተጨማሪም በአንድ በኩል አካባቢ ብጥበጣንና ውጥረትን የጎልውና መሠረት ያደረገውና ኢትዮጵያን መተናኮል፣ ማቁሰልና ማዳከም ሥራዬ-ብሎ የተያያዘው የአቶ ኢሣኢያስ አፈወርቂ አምባ-ገነን አገዛዝ በዚኽ ይዞታው መቀጠሉን ማስቆም የግድ የሚሆንበት፣ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ባሕር በር-አልባ ሆና መቀጠል የማትችል ከመሆኑ ጋር ተደማምሮ ሲታይ በሁለቱም አቅጣጫ ጉዳዩን በተጠቀሰው መልክ በሰላም መፍታት ካልተቻለ ከሰላማዊ መንገድ ውጭ ማስተናገድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ግዴታም ጭምር ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡ ይኸማ “ጦር-ሰባቂነት ነው” ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ በበኩሌ ግን ጦርነትን የግድ አይቀሬ የሚያደርገው ያለውን ሁኔታ በሰላም አለመፍታት እንጂ አደጋውን አስቀድሞ አስተውሎ ሰላማዊ መፍትኄ መፈለግ ጦረኝነት አይደለም፡፡ ለነገሩ ጦርነት መደረግ ካለበትና ትርጉም የሚኖረው የሰላም ደንቃራንና አይቀሬ ችግርን በማስወገድና የሕዝብን ዘለቄታዊ ጥቅሞች፣ ብሔራዊ ጥቅምንና ሰብዓዊ ክብርን ለማስጠበቅ ሊሆን ይገባል፡፡ ያ ደግሞ ብሔራዊ ግዴታ ይባላል፡፡ በእርግጥ ያንን ለማድረግ የማይናወጥ ብሔራዊ ስሜትን፣ ለሕዝብና ለታሪክ ከበሬታን፣ ከግልና ከቡድን ጊዚያዊ ጥቅማጥቅሞች ይልቅ አገርንና ሕዝብን ማስቀደምን፣ ቁርጠኝነትንና አስፍቶ ማየትን ይጠይቃል፡፡

እዚኽ ላይ ለሰላማዊ መፍትኄ አንደኛው ቀንደኛ ችግር አቶ ኢሣኢያስና ድርጅታቸው ሸዓብያ መሆኑ በተደጋጋሚ ሲገለጥ ምናልባት በአሁኑ ጊዜ በነአቶ መለስ ደጋፊነት የሚንቀሣቀሰው ፀረ-ኢሣኢያስ የኤርትራውያን ድርጅቶችን ስብስብ፣ አልፎም ሌሎችንም በመጥቀስ ጉዳዩ የአቶ ኢሣኢያስና የሸዓብያ ብቻ አይደለም ሠፋ ያለ ነው ሊባል ይችላል፡፡ አዎን ትክክል ነው፡፡ በበኩሌ የነአቶ መለስ ዜናዊን የአገዛዝ ሥርዓት መለወጥ አለበት የምለው የግድ ሰውዬው አቶ መለስ ስለ-ሆኑ ወይም ድርጅታቸው ሕወሓት ስለ-ሆነ ሣይሆን የቆሙበት የፖለቲካ ፍልሥፍናና እምነት፣ አስተሣሰብና አካሄዳቸው የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የአገር አንድነትና ብልፅግና፣ የሕዝብ ልዕልናና ደኅንነት ጠር ስለ-ሆኑ ነው፡፡ በእኔ እምነት ማንም ይኸንን የአፈናና የጭቆና፣ የልዩነትና የመከፋፈል መስመር የሚከተል ግለሰብ ሁሉ መለስ ዜናዊ፣ ቡድንም ሆነ ድርጅት ደግሞ ወያኔ ነው የምለው፡፡ እንደዚኹም የኤርትራን ሕዝብ መብቶች የሚያፍን፣ ሐይማኖትን፣ ቋንቋንና አካባቢን መሠረት ባደረገ የሚከፋፍል፣ የአፋር ሕዝብ ከሁለት ተከፍሎ እንዲቆይ የሚፈልግ፣ በትልቁም የኤርትራን ሕዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተገንጥሎ እንዲቀጥል የሚከጅል፣ የኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤትነት መብት የሚነፍግ አስተሣሰብ፣ ዓላማና እምነት ያለውና የሚያራምድ ሁሉ አቶ ኢሣኢያስን ተቃወመ አልተቃወመ እሱም ከኢሣኢያስና ከሸዓብያ ምድብ ነው፡፡ ታሪክና ደም ያስተሣሰራቸውን ኢትዮጵያውያንንና ኤርትራውያንን በሰው-ሰራሽ የልዩነት ግንብ ለመለየት መሞከርም ሆነ ለጠባብ የፖለቲካ ጠቀሜታና ጊዚያዊ ሥልጣን ሲባል አፍኖ እስከ-ወዲያኛው ለመቀጠል መሞከር የማይሆን አጉል ድካም ነው፡፡

ስለ-ሆነም ለኤርትራ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለበጎ ተስፋውና ዘለቄታዊ ጥቅሞቹ የቆመ፣ ኤርትራውያን ክብራቸውና ማንነታቸው ተጠብቆ ከቀረው ታሪክ ካስተሣሰራቸው ወገናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በወንድማማች/እህትማማች መንፈስ ሰላማዊ ግንኙነቱ እንዲቀጥል የሚፈልግ ዴሞክራት ኤርትራዊ ሁሉ ያለውን እንቅፋት አስወግዶ በሁለቱም በኩል ላለው ሕዝብ ሰላም መጠበቅና ዘለቄታዊ ጥቅሞች መከበር መሰል አስተሣሰብና እምነት ካላቸው ኢትዮጵያውያን ጋር መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ ሰላማዊ መንገዱ ይኸ ይመስለኛል፡፡

ከቅርብም ሆነ ከሩቅ የራሣችን ታሪክ ሂደቶችና ክስተቶች ስንነሣና በአሁኑ ጊዜ የዓለም-አቀፍ የዳበሩና እያደጉ የመጡ ኃይሎች የኃይል ምንጮችን ለመቆጣጠር ሲሉ ከተያያዙት ሽሚያ ላይ ያተኮረ እርብርብ እና ለዚኽና ለሌሎች ተዛማች ጥቅሞች ለማስጠበቅ ሲባል የፖለቲካ አሻራን ለመተው ከሚደረግ የመወዳጀት መባዘን፣ ኤርትራም በአላት ውሱን አቅም የምትገኝበትን ለውጭ ጥቃት ያጋለጠ ስትራቴጂያዊ ይዞታ የኤርትራ ሕዝብ ማንነትና ክብር ብቻዋን ማስከበርም ይሁን እንደ-አገር ቆሞ ለመቀጠል ቢያንስ አስቸጋሪ ነው፡፡ አንዳንድ ባዕዳን ኃይሎች አንፃራዊ ግዙፍነት ያላት ኢትዮጵያ እንደ ወትሮው በኤርትራ በኩል ያሉትን የቀይ-ባሕር ወደቦች በባለቤትነት መቆጣጠሯ በቀይ ባሕር አካባቢ የሚኖራቸውን ስትራቴጂያዊ ጥቅም እንደ-ልብ በማሣካቱ ረገድ እንደ እንቅፋት በማየትና የኤርትራን ሁለንተናዊ አቅም በመገምገምና እንደ-አገር ለመቆም የግድ የነሱን እርዳታ ስለሚያስፈልጋት *“ከእኛው ጉያ አትወጣም”* ከሚል ስሌት ተነስተው ኤርትራን ከኢትዮጵያ እንድትለይ ማድረጉ የብሔራዊ ጥቅማቸውን የማስከበር አካል አድርገው በመቁጠር አበክረው እንደተንቀሣቀሱ ይታወቃል፡፡ የውስጥ ብሶት ሰበብ መሆኑ ቢታወቅም ኤርትራ

በተገነጠለችበት መንገድና ሁኔታ ከኢትዮጵያ እንድትለይ የመደረጉ ዓብይ ምክንያትም ከዚያ ምክንያት የመነጨ መሆኑ ብዙ አጠያያቂ አይመስለኝም።

በእርግጥ ኢትዮጵያ የቀይ-ባሕር ወደቦቿን በባለቤትነት ስትቆጣጠር ምን ያኽል ኃያል አገር እንደምትሆን የኢትዮጵያን ጥንታዊ ታሪክ ለሚያውቅ ሁሉ ያ ዓይነት የባዕዳን ስሌትና ስጋት አያስገርምም። የሆኖ-ሆኖ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መለየቷ ጠቀሜታው ለኤርትራውያን እንዳልሆነ ያለፉት ሃያ ብኩን ዓመታት ያረጋገጡት ይመስለኛል። ምናልባት የኤርትራን እንደ-አገር ለመቆም ያለው ችግር ሲነሣ *"እንኳን ኤርትራ ጅቡቲስ እራሷን ችላ ትኖር የለም ወይ?"* የሚል አይጠፋም። ሁለቱን ማወዳደሩ ግን ዱባና ቅል ይመስለኛል።

በሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በኩል በባድመ ምክንያት ከገቡበት ያላስፈላጊ አጣብቂኝ ለመውጣትና ባድመን *"ለማስረከብ የተሰጠውን ውሳኔ በመርኅ ደረጃ ተቀብለነዋል"* ያሉትን በተግባር ለመፈጸም ሲሉ ምናልባት ከኤርትራ አምባ-ገነን አቻዎቻቸው ጋር *"አሰብን በተወሰነ ደረጃ በኪራይ ለመጠቀም የስምምነት ውል ተዋውለናል*" የሚል ዱብዳ ሊያፈልቁ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የነ "ወንድም" ጋዳፊ ድጎማ፣ የነ ሙባራክ ድጋፍና ማበረታታት፣ ወዘተ... የነጠፈባቸውና ከባድ ችግር ውስጥ የሚገኙት የኤርትራ አምባ-ገነኖች ኢትዮጵያ ለወደብ አገልግሎት የምታወጣውን ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ገንዘብ ከባድመ ጋር ካገኙ ይኽን አያደርጉም አይባልም። የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችም *"ይኼውና ያለ አንዳች ጦርነት አስፈላጊነት አሰብን መጠቀም አስችለናል*" በሚል ማደናገሪያ ለዚያ ሁሉ አሥርተ-ሽህዎች ማለቅ ምክንያት የሆነውን ባድመን አሣልፈው ሲሰጡ በአጠቃላይ ከኢትዮጵያውያን፣ በተለይ ከትግራይ ሕዝብ ዘንድ የሚኖርን ተቃውሞ ያን እርምጃ በመውሰድ "በማካካሻነት" ለማድበስበስ ቢሞክሩ የማይሆን ነው ማለት አይቻልም።

*መቸም* አምባ-ገነንኖች ቅድሚያ የሚሰጡት ለሕዝብ ነፃ መሆንና ደኅንነት ሣይሆን የኀልውና ዋስትና አድርገው ለሚቆጥሩት ሥልጣን ስለ-ሆነ፤ አሁን በኤርትራ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ያለው ገዥ ቡድን (ሸዓብያ) መሪዎች በሥልጣን ላይ ለመቆየት በሚደርጉት መውተርተር ባለ አቅማቸው ሁሉ በኤርትራ ሕዝብ ላይ የዘረጉትን አፈናና ያሰፈኑትን የሽብር ሥርዓት ማጠናከር ብቸኛ ምርጫ አድርገው እንደሚወስዱ ሳይታለም የተፈታ ነው። የሸዓብያ መሪዎችም በሥልጣን ላይ ለመቆየት ቀላል ወጭ የማይጠይቀውን የአፈናና የመጨቆኛ መዋቅሮቻቸውን ለማጠናከር ሲሉ በሚወዷቸው እርምጃዎች ባዕዳንን የሙጥኝ ማለታቸውና የኤርትራን ሕዝብ ኀትተው የባዕዳን ጥገኛ የሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ ሊያስገቡት ስለሚችሉ፤ የሚባለው ነፃነት ይበልጥ ትርጉም-የለሽ ሊሆን የመቻል ዕድሉ ሠፊ ነው። ስለ-ሆነም፣ የኤርትራ "ነፃነትም" ሆነ የኤርትራ ሕዝብ መብት የሚገሠሠው ኢትዮጵያ <u>ወገን ከሆነው የኤርትራ ሕዝብ ጋር በሚደረግ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ስምምነት</u> በቀይ-ባሕር በር/ጠረፍ ላይ የባለቤትነት መብቷን ማግኘቷና ማስከበሯ ሣይሆን የኤርትራን ሕዝብ ሊበትንንና ለትርምስ ሊዳርግ የሚችል ለፈነዳ የደረሰ ከፍተኛ ውጥረትና ለባዕዳን ጥገኛ የሚያደርግ የአፈና ይዞታና ሁኔታ እንደሆን ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ይመስለኛል።

ቀደም-ሲል እንደተጠቆመው ኢትዮጵያ ለምሣሌ የበርበራን ወደብ ከመጠቀም ባለፈ በኤደን ባሕረ-ሰላጤ በኩል የባሕር በር ሊኖራት በሚያስችል መልኩ ሶማሌላንድ በመባል የሚታወቀው የሰሜን-ሶማሌ ክፍል በአንድ መንግሥታዊ ትሥሥር/መዋቅር ሥር የመሆን ዕድል እንዳለ ከራሣቸው ከሶማሌላንድ ተወላጆች ቀጥታ ጥያቄ እንደቀረበ፣ ሆኖም እነ አቶ መለስ ዜናዊ አሻፈረን እንዳሉ፣ መረጃዎች አሉ። የሆነ-ሆኖ ያ እንዳለ ሆኖ በቀይ-ባሕር በኩል ያለው ከአጠቃላይ ስትራቴጂያዊ ግብአቱና ተፈላጊነቱ፣ ከአፋር ሕዝብ የአንድነት መብትና ጥያቄ፣ እንዲሁም በሁለቱም በኩል ካለው የሕዝብ ትሥሥርና ታሪክ ጋር በአዎንታዊነቱ፣ ተለያይቶ መቆየቱ ደግሞ ከሚኖረውና ከሚያስከትለው ክብደቱ ከፍ ያለ የአሉታዊነት ጎኑ አኳያ በማየት ነው ለቀይ-ባሕር ጠረፍ ለየት ያለ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የምለው።

ከጅምሩ ለመጥቀስ እንደ-ሞከርኩት ይኽን አጭር መንደርደሪያ ያቀረብኩት የጉዳዩን አሣሣቢነት ለማስገንዘብና ሰላማዊ መንገድ ካልተገኘለት ግጭትን የሚጋብዝ በመሆኑ ከወዲኹ የሰከነ ውይይትና ምክክር ማድረጉ አስፈላጊ ነው ከሚል ነው። ካለፈ ፈተና የበዛበት ታሪካችንና አሁን ያለ ዙሪያ-ጥምጥም ችግሮች በመነሣት ኢትዮጵያውያን የባሕር በር ጥያቄን ሊያዩት የሚገባው ከአገራቸው አንድነት፣ ከሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ መሆኑ አዲስ ሊሆንም ሆነ ሊገርም ከቶ አይችልም።

ወገን ከሆነው የኤርትራ ሕዝብ ጋር በሚደረግ '**ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ስምምነት**' እንዴት ኢትዮጵያን የባሕር በር ባለቤት ማድረግ እንደሚቻልም ሆነ እንዲለያይ የተበየነበት ሕዝብ በምን መልክና ሁኔታ በሂደት ወደ-አንድነቱ እንደሚያመራ በተለየ የማቀርበው ይሆናል።

አያል-ሰው ደሴ (ሰኔ፣ ሁለት-ሽህ-ሦስት ዓ/ም)